***የጎንደር ዕድርና መረዳጃ ማኅበር ጽሕፈት ቤት በሲያትል፤***
***Gonder Mutual Association of Seattle***
***1123 East Spruce Street***
***Seattle, WA 98122***
***Tel: (206) 762-5195***

---

**እኛ በሲያትል ዋሽንግተን የጎንደር ዕድርና መረዳጃ ማኅበር አባላት፣ወያኔ በሀገራችን ኢትዮጵያ ላይ ከዚህ ቀደም ያደረሰውንና አሁንም በማድረስ ላይ ያለውን በታሪክ ተወዳዳሪ የሌለው ጥፋቱን በጥብቅ እንቃወማለን።**

**በተለይም ከ**1600 **ኪሎ ሜትር ርዝመት እስከ** 50 **ኪሎ ሜትር ስፋት ያለውን የሀገራችንን ለም መሬት ለሱዳን መንግሥት መስጠቱ ሲጋለጥ፥ወያኔ ኢትዮጵዊ ባሕርይ የሌለው ፍጹም ከሀዲ መሆኑ ጥርጥር የሌለው ሐቅ ሁኗል።**
**ወያኔ የተነሣለት ዐላማ፥ አንድን ዘር ነጻ ለማውጣት ሲሆን፥ በዘር በሽታው ደንዝዞ፥ በአንድ ጭንቅላት ብቻ እየተመራ የንጹሀንን ደም ማፍሰስ፥ ለብዙ ሽህ ዘመናት የኖረች ሀገርን ማፈራረስ የዘወትር ተግባሩ ሁኗል።**

**የወያኔ ሰለባዎች የጎንደር ሕዝብና የትግራይ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን በመላው ኢትዮጵያዊ ላይ የተነጣጠረና፥ሀገርን የማፈራረስና ብሎም ፈጽሞ የማጥፋት ተግባር መሆኑን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሊረዳውና ሊገነዘበው የሚገባ ሐቅ ነው።**

**በተለይም የጎንደር ሕዝብ፥በብዙ ሽህ የሚቆጠር የሕይወት መሥዋዕትነት በጠገዴ፥በወልቃዪትና ጸለምት፥እንዲሁም በሌሎቹም በመከፈል ላይ ያለ ሲሆን፥ በራሱ መሬት መቃብር እንኳን ተከልክሎ፥ያለማውን ባድማ፥ የሠራውን ቤት ተቀምቶ፥ለስደት ለምርኮና ለግዞት ተዳርጎ ይገኛል።**

**ወያኔ በቅርቡ በይፋ የተጋለጠበት ለሱዳን የመሬት ስጦታ ደግሞ፥የኢትዮጵያን ሕዝብ ሕልውና የመጨረሻ አደጋ ላይ እንደሚጥል ምንም ጥርጥር የለውም።**
**ጎጠኛው ወያኔ በስሙ የሚነግድበት የትግራይ ሕዝብ፥ለመብቱ የታገሉለትና የተዋደቁለት ዛሬ ከጎኑ የሉም። ለኢትዮጵያዊነት ቀድመው የሚሰዉ አባቶች የወያኔ የመጀመሪያው ሰይፍ ሰለባዎች በመሆን፥አንድ በአንድ በተራ ተለቅመው አልቀዋል። ወያኔ ጠባብ ዘረኛ በመሆን ብቻ የትግራይን መሬት ያስከብር እንጅ፥የትግራይን ሕዝብ መብት ግን ፈጽሞ ገፍፎታል።**

**እኛ የጎንደር ዕድርና መረዳጃ ማኅበር አባላት፥ከአብራኩ የወጣነው ሕዝባችን በአረመኔው ወያኔ እየደረሰበት ያለውን በደል ጠንቅቀን እናውቃለን።ወያኔ ለመፈጸም ባቀደው ከሁመራ እስከ ጋምቤላ፥የመሬት ችርቻሮ በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ተፈናቅለዋል፤ ወያኔን የሚመራው አንድ ጭንቅላት፥የሚናገረው ሁሉ፥አንድም እውነት የሌለው መሆኑን በደልና ግፍ በሚፈራረቅበት ወጋናችን ስም እንመሰክራለን።**
**ከዚህም ሌላ በወያኔና በሱዳን በጣምራ ጦር በግፍ ደሙ በመፍሰስ ላይ ያለውን የሕዝባችንን ጩኸት ለዓለም ማሰማት ብሔራዊ ግዴታችን ነው።**

እኛ በሲያትል የምንገኝ የጎንደር እድርና መረዳጃ ማኅበር አባላት፥ከአብራኩ ለወጣነ ው ሕዝባችን፥ብሎም ውድ ሀገራችን ኢትዮጵያን ለማዳን፥የሚያስፈልገውን መሥዋዕት ነት ሁሉ ለመክፈል ዝግጁነታችንን እናረጋግጣለን።

የጎንደር ዕድርና መረዳጃ ማኅበር አባላትና ጥሪ የተደረገላቸው ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያ ውያን በተገኙበት በ06-15-2008 ስለ ሀገራችንን ወቅታዊ ሁኔታዎች ባደረግነው ስብሰባ የሚከተሉትን ውሳኔዎችንና ጥሪዎችን እናስተላልፋለን።

1ኛ. ቅጥረኛው ወያኔ የኢትዮጵያን መሬት ለባዕዳን ለመስጠት ሕጋዊም ሆነ ሞራላዊ ብቃትና መብት የለውም።

2ኛ. ዘረኛው ወያኔ በጉልበት ወደ ትግራይ የከለላቸውን የወልቃዪት ጠገዴንና የጸለምትን ክልሎች እንዲመልስ፥የክልሉ ባለቤት የሆነው፥የወልቃዪት የጠገዴና የጸለ ምት ሕዝብ በክልሉ የመኖር መብቱ እንዲከበር።

3ኛ. የትግራይ ሕዝብ ልዩ በሆነ የታሪክ ግዳጅ ምዕራፍ ላይ ይገኛል። ይህ ልዩ ታሪካዊ ግዳጅ፥ከሕይወታቸው ይልቅ ሀገራቸው ኢትዮጵያን ለማስከበር ታላቁ መሪያች ን አጼ ዮሐንስ፥የተሰዉበትን ምድር ማስከበር ነው። በዚህ አጋጣሚ የታሪክ ምዕራፍ፥ የጎንደር እድርና መረዳጃ ማኅበር አባላት፥በጎንደር ሕዝብ ስም፥ለትግራይ ሕዝብ ታሪ ካዊ ግዴታህን እንደትወጣ እና ለክፉ ቀን ደራሽህ ለሆነው ወገንህ ለጎንደር ሕዝብ ከጎ ኑ እንድትቆም ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

4ኛ. የአንድ ሀገር የጦር ሠራዊት ዋነኛና የመጀሪያው ተግባር የሀገርን ዳር ደን በር ማስከበር ነው። የኢትዮጵያ መለዮ ለባሹ ሠራዊት ብሔራዊ ግዴታውን እንዲወጣ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

5ኛ. በመላው ዓለም ለምትገኙ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን፤ ሀገራችን ኢትዮጵያን ለማዳን በያለንበት በግልም ሆነ በማኅበር፥በእምነት ቦታዎችና በሀገር አቀፍ በመደራጀት ሀገራችንን እንድንታደግ፥በሚያስፈልገው ሁሉ ለወገኖቻችን በአፋጣኝ እንድንደርስላቸው ብሔራዊ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

በጀግኖች ልጆቿ ለዘመናት ታፍራና ተከብራ የኖረች ሀገራችን ኢትዮጵያ፣ ዛሬም በቆራጥ ልጆቿ ዳር ደንበሯ ተክብሮ ለዘለዓለም ትኖራለች!

**ከጎንደር ዕድርና መረዳጃ ማኅበር፤**
**ሲያትል፥ዋሽንግተን፤**
**June 15, 2008**